# የደቡብ ኦሞ ዞን አቅም ግንባታ መምሪያ በ2001 ዓ.ም የ9 ወራት ሪፖርት

የዞናችንን ህዝቦች ከኋላቀርነትና ድህነት ህይወት በማላቀቅ፣ መልካም አስተዳደር በማስፈን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት በማምጣት ከልማቱ ህዝቡ በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ የሚሆንበትን የልማትና ደሞክራሲ ሥርዓት ለመገንባት የማስፈፀም አቅም ግንባታ ሥራዎች ወሣኝ ሚና እንደሚጫወት በማመን መምሪያው የ3 ዓመት የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራቴጅክ ዕቅድን መሠረት በማድረግ በ2001 በጀት ዓመት በተለይም በታችኛው የህ/ሰብ ክፍል መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የአቅም ግንባታ ኘሮግራሞችን ቀጣይነትና ዘላቂነት ባለው ሁኔታ ለመተግበር ቅንጅታዊ የማስፈፀም አቅም መፍጠር ቁልፍ ውጤትና የትኩረት አቅጣጫ አድርጎ ሲንቀሣቀስ ቆይቷል ፡፡

ባለፋት ዘጠኝ ወራት ከአሥራ አስምቱ የአቅም ግንባታ ኘሮግራሞች መካከል በዞንና በወረዳ ትኩረት ከተሰጣቸው የሲቪል ሰርቪስና ፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ በወረዳ አቅም ግንባታ ፤ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ እና መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለዉጥ ኘሮግራሞች ዙሪያ የተያዙ ዕቅዶች ተፈፃሚ እንድሆኑ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በፕሮግራሞች የተከናወኑ ዝርዝር ውጤቶች እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡

## 1. መሠረታዊ ሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ በተመለከተ የተፈጸሙ ዝርዝር ውጤቶች

- መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥን በሰባት ዞን ሴክተር መ/ቤቶች፣በ8ቱ ወረዳና 1ከተማ አስተዳደር ሙሉ ትግበራ መግባት እንዲችሉ ለ3838 አመራርና ሰራተኞች በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለዉጥ ፅንሰ ሃሳብ፤በለዉጥ አመራር እና በማስፈፀም አቅም ግንባታ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ላይ ስልጠና በመስጠት ወደ ሙሉ ትግበራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡
- በሰራተኞች ድልድል ደንብ ቁጥር 72/2001 መሰረት ጥናቱ በተካሄደባቸውና ወደ ሙሉ ትግበራ በገቡ ሰባት ሴክተሮች የ567 ሰራተኞች ድልድል ተካሂዷል፡፡ የተመደቡ አስተባባሪዎችና ፈጻማች በተለያዩ ጊዜያት ስለ ሥራ ሂደቱ በክልል፤ በዞንና በወረዳ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡
- ያልተደለደሉ 261 ሠራተኞች በደንብ ቁጥር 72/2001 መሠረት የተለያዩ አማራጭ መፍትሄዎች ተሰጥቷቸው እየተስተናገዱ ይገኛሉ፡፡
- በዞን ሰባት ሴክተር መ/ቤቶች ቼክ ልስት ተዘጋጅቶ በአዲሱ ሥራ ሂደት አተገባበር ላይ 4 ዙር ድጋፍ፣ምክርና እገዛ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት፣ንግድ ኢንዱስትሪ፣ፖሊስና ትምህርት መምሪያዎች በለውጡ አበረታች ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡
- ለወረዳዎች ድጋፍ፣ምክርና እገዛ ዞን ማእከል በመጥራት በደብዳቤ እና በስልክ ተሰጥቷል ፡፡
- በዞን መሠረታዊ ሥራ ሂደት ለውጥ ተግባራዊ ያደረጉ በ7 ሴክተር መ/ቤቶች 212 የተፈቀደ መዋቀር ሲኖር፣ ከተፈቀደ መዋቀር 97 /44.33%/ ሠራተኛው የተደለደለበት ሲሆን ቀሪው 118/55.66%/ ክፍት መደብ ነው፡፡ በወረዳ ወደ ሙሉ ትግበራ የገቡትን በተመለከተ፡-

ኛንጋቶም 20% ፤ ሰሜን አሪ 43.9%፤ በበና ፀማይ 54.75%፤በሐመር 69.64%፤ ማሌ 45.4% ፤ደ/አሪ 32.69%፤ዳሰነች51.6፤ሳላማጎ30.76% ጂንካ ከተማ56.25% የሰው ኃይል በማሟላት ወደ ሥራ ገብቷል፡፡

- ❖ በየመ/ቤቶች ሙያ መስመራቸው ባለመኖርና በአግልግሎት ማነስ አምስት ሰዎች በዞን መፍትሄ አማራጬች አስተግባሪ ግብረ ኃይል አማካይነት ዝቅተኛ መስፈርት ወደምያሟሉበት መ/ቤት ሽግሽግ ተደርጓል፡፡
- ❖ መሠረታዊ ሥራ ሂደት ተግባራዊ በተደረገባቸው መ/ቤቶች ስሥራ ሂደቱ አመቺ የሆነ አከባቢ እንዲፈጠር ስማድረግ በየተቋሙ ያሉ የሥራ ሂደቶች በአንድ ክፍል እንዲደራጁና የሥራ ሂደቱ ተፈፕሮሃዊ ፍሰቱን በጠበቀ ሁኔታ እንዲተገበር በቢሮ ዝግጅት፤ቁሳቁስ በማሟላት፤ስልጠና በመስጠትና በጀት በመመደብ ብርቱ ጥረት ተደርጓል፡፡

## 2. . የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን በተመለከተ የተፈጸሙ ዝርዝር ውጤቶች

እየተገበረ ያሉ 5ቱ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን ሙሉ በሙሉ በመ/ቤቶች በተቀናጀ መልኩ እንድተገበር ለማድረግ ውይይቶች ተደርጓል፡፡በሲቪል ሰርቪስ ፕሮግራሞች መሠረት ለሠራተኞች የተሰጠዉ ዉጠት በሠራተኛው ድልድል ወቅት እንደ አንድ መመዘኛ ሆኖ እንድተገበር ድጋፋዊ ክትትል ተደርጓል፡፡ በ5ቱ ማሻሻያ ፕሮግራሞች የተከናወኑ ዝርዝር ውጤቶች እንደሚከተለዉ በዝርዝር ቀርቧል፡፡

### 2.1 አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ፕሮግራም

- ❖ ከዞን እስከ ወረዳ ባሉት የመንግሥት መ/ቤቶች የአገልግሎት አሰጣጥ "Quick wins" ሥራ ላይ እንዲውል በአንደኛ ሩብ ዓመት ለዞን መ/ቤቶች፣ ለ8ወረዳና ለ1ከተማ ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- ❖ አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ለዞን መ/ቤቶች ቼክ ሊስት ተዘጋጅተው ድጋፊና እገዛ ተደርጓል፡፡ አገልግሎት አሰጣጥ እንደሥርዓት ለመትከል በመሠረታዊ አሰራር ሥርዓት ለውጥ መሠረት የአገልግሎት አሰጣት ፕሮጀክት ተዘጋጅተዋል፡፡
- ❖ ማሻሻያውን እንደሥርዓት ለመትከል ማሌ፣ኛንጋቶም፣ሐመር፣ዳሳነችና በና ፀማይ ወረዳ ፕሮጀክቱን ከሴክተር መ/ቤቶች ጋር ተፈራርሞ ወደ ሥራ ገብቷል፡፡
- ❖ በሁሉም መንግስት ተቋማት የተገልጋይ ቅሬታ ለማስተናገድ ሥርዓቱን ለመዘርጋት 100% በዞን ሴክተር መ/ቤቶች፣ በ8 ወረዳዎችና በ1 ከተማ አስተዳደር የተገልጋይ ቅሬታ ማስተናገጃ አካላት ተቋቁሞ በቅፃቅጾቹ መሠረት ተገልጋዮች እየተስተናገዱ ነው፡፡ ከተለያዩ መ/ቤቶች ሃያ አቤቱታዎችና ቅሬታዎች ቀርበው በቂ ምላሽ አግኝተዋል፡፡የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓት ማቅረቢያ ፎርማት ለተገልጋይ አመቺ ሁኔታ እንድቀመጥ ጥረት ተደርጓል፡፡

## 2.2 የሰው ኃይል አስተዳደር ማሻሻያ ፕሮግራምን በተመለከተ

- ❖ ማሻሻያ ፕሮግራሞች በተቀናጀና በተዋሃደ ሁኔታ ዘላቂነታቸውን ለመጠበቅ የማወዳደርያ ሰነድ ተዘጋጅቶ ወረዳዎችችና ዞን ሰክተር መ/ቤቶች በሪፎርም አፈጻጸማቸው መልካም ውጤት ያስመዘገቡ ተሸልሚል ::
- ❖ 100% በሁሉም መንግሥት ተቋም የውጤት ተኮር ስርዓት እንድዘረጋ ድጋፍ ተደርጓል እንዲሁም የውጤት ተኮር ዕቅድ አፈጻጸም በመሰረታዊ የሥራ ሂደት ጥናት በሠራተኛው ድልድል ወቅት እንደ አንድ መመዘኛ ሆኖ እንድተገበር ድጋፋዊ ክትትል ተደርጓል፡፡
- ❖ ለሁሉም ወረዳዎች የዕቅድ ኦረንቴሽን በመስጠት ዕቀዳቸውን እንዲያዘጋጁ ድጋፍ ተደርጓል የውጤት ተኮር ዕቅድ እሰከ ምዘና እንዲሰራበት ተደርጓል፡፡
- ❖ የመምሪያው የሰዉ ሃብት ዕቅድ ተዘጋጅቶ በስታንዳርዱ መሠረት ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል፡፡
- ❖ በዞን መሠረታዊ ሥራ ሂደት ለውጥ ተግባራዊ ባደረጉ በ7 ሴክተር መ/ቤቶች 118/55.5%/ እና በ8 ወረዳዎችና በ1 ከተማ አስተዳደር 588 ክፍት መደቦች ተለይተዋል፡፡
- ❖ በሰሜን አሪ ወረዳ ያስአግባብ የተፈጸመ ቅጥር እንዲሰረዝ ተደርጓል፡፡
- ❖ በህግ ሙያ የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ለመቅረፍ በተያዘው ዕቅድ መሠረት ከአርብቶ አደር አከባብዎች 50 ዕጩ ሰልጣኞች ተመልምለዉ ስማቸው ለክልል አቅም ግንባታ ተላልፎ ጥሪ በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ፡፡
- ❖ መሠረታዊ ሥራ ሂደት ለውጥ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ያደረጉት አደረጃጀታቸውን ለመለወጥና ቢሮሃቸውን ምቹ እንዲያደርጉ ተደርጉ ተግባራዊ ሆኖሃል፡፡
- ❖ የ2000 ዓ.ም. የ40 መ/ቤቶች የሠራተኞች መረጃ ተሰባስቦ ተደራጅቷል፡፡
- ❖ በሰው ሃብት ልማት 17 ባለሙያዎች ለመጀመሪያ ድግሪ ፣ 4 ባለሙያ ለሁለተኛ ድግሪ በድምሩ 21 ባለሙያዎች ለረጅም ጊዜ ስልጠና በዕጩ ተመልምሎ ጥሪ እየተጠባበቁ ነው፡፡

## 2.3 የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ማሻሻያ ፕሮግራምን በተመለከተ

- ❖ የጨረታና የግዥ አፈጻጸም ግልጽና አሰታፍ እንድሆን በዓመት ሁለት ጊዜ በዕቅድ በተደገፈ መልኩ እንዲፈጸም ጥረቶች ተደርጓል፡፡
- ❖ ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ተካሄዷል፡፡
- ❖ ከአገልግሉት ውጪ የሆኑ ንብረቶች በአጣር ኮሚቴ በመለየትና አጠቃቀማቸው በማስጠናት ተሸጠው ለመንግሥት ገቢ እንደሆን ተደርጓል::
- ❖ በሰሜን አሪ በ4 ሴክተር መ/ቤቶች ያስአግባብ የተፈጸመ የደረጃ ዕድገት ክፍያ በዞን አቅም ግንባታ መምሪያ ሠራተኛ መከታታያ ቡድን ተፈትሾ 19,112.00 / አስራ ዘጠኝ ሺ አንድ መቶ አስራ ሁለት ብር/ ተመላሽ እንድሆን ተደርጓል፡፡

## 2.4 የሥነ ምግባር ማሻሻያ ፕሮግራምን በተመለከተ

- ❖ በየመ/ቤቱ ሠራተኞች፣ዘርፎችና ክፍል ኃላፊዎች የስነ-ምግባር መርሆችን በመስጠፍ ግንዛቤ ጨብጠዉ እንድሰሩ ተደርጓል::
- ❖ በሰሜን አሪ ወረዳ የስነ-ምግበር ችግር ባለባቸው / የሥራ ሰዓትን በማሸራረፍና መደበኛ ስራቸው ላይ በማይገኙ/ የሴክተር መ/ቤት ሠራተኞች ላይ እርምጃ እየተወሰደ ነው፡፡
- ❖ በማሌ ወረዳ በ22 ቀበለተያት ለ800 ህብረተሰብ ክፍል በስነ-ምግባር መርሆች ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- ❖ በደቡብ አሪ የስነ-ምግባር ትምህርት ከተለያዩ ስልጠናዎች ጋር በማቀናጀት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ተገልጋይ ህብረተሰብ መብትና ግደታውን እንዲያዉቅ ቅድሚ ዝግጅቶች በማከን በፋይናንስና በፍትህ ጽ/ቤቶች እየተሰራበት ነው፡፡

## 2.5 የበላይ ሥራ አመራር ማሻሻያ ፕሮግራምን በተመለከተ

- ❖ ደንቦችና አዋጆች ላይ ሠራተኛውን በማወያየት ግንዛቤ የማስጨበት ሥራ ተሰርቷል፡፡
- ❖ ስትራቴጂክ ዕቅድ አመራርና ዓመታዊ ዕቅድ አሠራር ሥርዓት በሁሉም የመንግሥት ተቋማት በማስተሳሰር ተግባራዊ እንዲሆን ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በሁሉም ሴክተሮች ስትራቴጂክ ዕቅድ ተከልሷል፡፡
- ❖ የፐብሊክ ሴክተር አቅም ፕሮግራሞች ዕቅድ አፈፃፀም ላይ ለዞን መ/ቤቶችና ለወረዳዎች ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- ❖ የፐብሊክ ሴክተር አቅም ፕሮግራሞች ዕቅድ ዝግጅት ስይ ለሁሉም ወረዳና ለዞን መ/ቤቶች ክትትልና ቴክኒክል ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- ❖ ከወረዳ ወደ ዞን የሚላኩ የዓመት ዕቅዶችና ሪፖርቶች በጊዜ እንድደርሱ ለወረዳዎች ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ማሌና በና ፀማይ ወረዳ በጊዜ ከሚልኩት ተጠቃሽ ናቸው፡፡
- ❖ በምልመላና መረጣ መመሪያ ላይ ኢንስፔክሽንና ድጋፍ ለማድረግ በተያዘው ዕቅድ መሰረት በወረዳዎች ላይ በ10 ጽ/ቤቶች የኢንስፔክሽን፣ በ3 ጽ/ቤቶች ላይ ድጋፍና ክትትል ስራ ተሰርቷል፡፡

## 3. መልካም አስተዳደርን በተመለከተ

- የአርብቶ አደር አካባቢ መልካም አስተዳደር ፓኬጅ ዝግጅቱ ተጠናቆ ረቂቁ ለአርብቶ አደር ወረዳዎች ተልኮ ግብረ-መልስ ተሰባስቦ ወደ ክልል ተልኳል፡፡
- የመልካም አስተዳደር መርሆችን እንደስርዓት ለመትከል በተዘረጋ አሰራር በዞን ፍትህ መ/ቤቶች በአዲሱ አሰራር ሥርዓት ስውጥ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮጀክቶች ተዘጋጅል፡፡
- በወረዳና በዞን መልካም ተሞክሮን መቀመር ይቻል ዘንድ በዞን ደረጃ አብይ ኮሚቴና ቴክኒክ ኮሚቴ ተቋቁሞ የመቀመሪያ ሰነዱ ለሁሉም ወረዳዎች ተልኮላቸዋል ኦሪንቴሽንም ለወረዳዎች አቅም ግንባታ ኃላፊዎች ተሰጥቷል፡፡
- የመልካም አስተዳደር ግድፈቶችን በማስተካከል ቅሬታን በመፍታት በዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አበረታች ሥራ ተሰርቷል፡፡
- በወረዳ ደረጃ ምርጥ ተሞክር ቀምሮ ወጥ በሆነ መንገድ ማዘጋጀት በሰነዱና በአሠራር ስልቱ ግንዛቤ ማስጨበጥ በሁሉም ሴክተር መ/ቤቶችና ቀበሌያት ሥራውን ተግባራዊ በማድረግና በማስፋፋት ከፍተኛ የአፈፃፀም ደረጃ እንዲመዘገብ ለማስቻል እየተሰራበት ነው፡፡በዚህም መሠረት በበና ፀማይ፣በሐመር፣ በማሌና በደቡብ አሪ ምርጥ ተሞክሮ የመቀመር ሥራ ተከናውኗል፡፡
- በማሌ ወረዳ ለ820 ህብረተሰብ ክፍል በጀንካ ከተማ አስተዳደር ለ85 ቀበሌ አመራር በሰ/አሪ ለ231 ሥራ አስከያጆች በ8ቱ መልካም አስተዳደር መርሆች ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡በእያንዳንዱ መልካም አስተዳደር መርሆች የተከናወኑ ሥራዎች እንደሚከተል በዝርዝር ቀርቧል፡፡

### 1. ተሳትፎፏዊ መርህን በተመለከተ

- የመልካም አስተዳደር ሰፊ ችግሮችን ለመፍታት በየደረጃ በተሰጠ ስልጠና ለችግሮቹ የጋራ መፍትሄ በማምጣት ህብረተሰቡ በተግባራዊ እንቅስቃሴ በልማት ሥራ በአንድ ዓላማ ከሐሳብ ጀምሮ እስከ ተግባር በምገባ በመሳተፊና አምና ባለቤት በመሆን ህዝቡ እራሱ መድረክ ፈጥሮ በመሳተፍ ለልማት ስራ ቁሳቁስ ለማሰባሰብ ተወያይተው በጋራ ተሳትፎ መንገድ ተሰርቷል፣ ት/ቤት ተሰርቷል፣ ጤና ኬላ ተሰርቷል፣ ለልማት ሥራ በጉልበት አስተዋፅኦ ተደርጓል፡፡ በዚህም በበና ፀማይ ጎልዲያ ቀበሌ፣ በማሌ ባላ ቀበሌ፣በደቡብ አሪ አልጋና ሺጾ ቀበሌዎች ተጠቃሾች ናቸው፡፡እንዲሁም በበና ፀማይና በሰሜን አሪ ወረዳ በህብረተሰቡ ተሳትፎ የመምህራን መጠለያ ሰርቪስ በቀበሌ የተሰራ ሲሆን ይህ መልካም ተሞክሮ ተደቷል፤

- በጋራ ተሳትፎ የመምሪያው ሠራተኞች ከሐሳብ እስከ ተግበር በመሳተፍ በማቀድ በኤች አይ ቪ ኤድስ ወላጆቻቸውን ላጡት ህፃናት እስኪሪብቶ ገስተው በምማሩበት ትምህርት ቤት በመነሄድ አሰራጭቷል፡፡

- በገጠር መልካም አስተዳደር ችግሮችና መፍትሄዎች ላይ ግንዛቤ በመያዝ ህብረተሰቡን በማሳተፍ ዕቅድ በማቀድና በመገምገም በጀት አመደደብና አጠቃቀም በሠስዳ ለህብረተቡ በማሳወቅ በተግባራዊ እንቅስቃሴ ስራውን በመከታተልና በጋራ ተሳትፏነትን ፈጥሮ በመስራት ማሴ ወረዳ በአርዓነት ይጠቀሳል፡፡
- ወንጀል የመከላከል ሥራ በተሰጠው ስልጠና ግንዛቤ በመያዝና በአንድ ዓለማ በመሰማማት ኮሚዩኒቲ ፖሊስንግ ለማስፋፋትና ለማጠናከር በቀበሌ ደረጃ የተሰራ አኩር ተሳትፎሃዊነት የተለበሰ ስራ በማሌና በበና ፀማይ ወረዳ ተከናዉኖሃል፡፡

## 2. <u>የጋራ መግባባት መርህን በተመለከተ</u>

- በዞን መ/ቤቶች የጋራ መግባባትን በተመለከተ ሠራተኞች ዕቅድ በጋራ አብሮ ከማውጣት እስከ መገምገም ድረስ አብሮ እንዲሰሩና የጋራ ራይዕናግብ እንድይዙ በመርሆ ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በተዘረጋ አሰራር በተሰጠ ስልጠና ህብረተሰቡ የጋራ ግብና የጋራ አመለካከት በመያዝ በመግባባት የተሳያዩ የልማት ሥራዎችን በማከናወን ግንባር ቀደም የሆኑት በሐመር ወረዳ የሻንቆ ቀበሌ ህብረተሰብ ሲሆኑ በዕቅድና አፈፃፀም ዙሪያ ህዝቡና ባለሙያው በጋራ እየተወያዩ የሚተገበር ሲሆን ሙያተኞችን በሙያ ዘርፋቸው ወደ መንደር በመዝለቅ ህዝቡን በመደገፍ አበረታች የመልካም አሰተዳደር ሥራ ተከናውኖሃል፡፡
- ህብረተሰቡ በግል ሥራው ሆነ በጋራ ከማቀድ እስከ ፍፃሜው በጋራ በመግባባት በደቡብ አሪ ወረዳ በአልጋ ቀበሌ በኤች.አይ.ቪ ወላጆቻቸውን ሳጡ እርሻ በማረስ እንዲሁም በግብዓት አጠቃቀምና የተለያዩ የልማት ሥራ በጋራ በመግባባት የተሰራ የመልካም አስተዳደር ሥራ ወደ ሌሳ ሲስፋፋ የሚገባ መልካም ተሞክሮ ነው፡፡

## 3. <u>ቶሎ ምላሽ መስጠት መርህን በተመለከተ</u>

- የመልካም አስተዳደር መርሆችን ወደ ተግባር በመተርጎም በመምሪያው ተጨባጭ ችግሮች ከዞን መ/ቤቶችና ከወረዳ የቀረቡ 20 አቤቱታዎችን በፅሞና በማየት ለተጨባጭ ችግር በመጨነቅ በወቅቱ ቶሎ ምላሽ በመስጠት ሥራ ተሰርቷል፡፡
- ለህዝቡ ጥያቄ ቶሎ ምልሽ ለመስጠት ያለው መርሆ ላይ ግንዛቤው በመያዝ የህዝብ ጉዳዮች በአንዛኛው ቀበሌ ቶሎ ምላሽ ይሰጥበት ዘንድ ባለጉዳይ በቀጠሮ እንዳይመላለስ በቀበሌ ደረጃ በሣምንት አንድ ቀን /በተወሰኑ ቀበሌዎች አርብ፣ በሌሎቹ ሐሙስ / ባለጉዳይ የሚስተናገድበት ቀን ሆኖ የተወሰ ሲሆን በወረዳ ደረጃ አስተዳደር ሰኞ፣ ረቡዕ ጠዋት ሲሆን በሴክተር ደረጃ ትምህርትና ጤና ጽ/ቤቶች ባለጉዳይ ማስተናገጃ ፕሮግራም አሳቶ በዚህም ደቡብ አሪ በአርዓነት የሚጠቀስ ሥራ ተይቷል፡፡

## 4. <u>ግልጸኝነትና</u>

- ህብረተሰቡ በቂ መረጃ በማግኘትና ግልጸኝነትን ለመፍጠር በመምሪያው የስራ እንቅስቃሴ በመገናኛ ብዙኃንና በፕሬስ ለመግለፅ በተያዘው ዕቅድ መሠረት የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት በተሰሩ ስራዎች ሳይ ለደቡብ ኤፍ. ኤም. 100.9 ጋዜጠኞች መግለጫ ተሰጥቷል፡፡
- በተሳያዩ ጊዜ የተሰጠ ስልጠና ሥራ ሳይ በማዋል ግልጸኝነት መርሆ ወደ ተግበር በመተርጎም የተደለደለውን በጀት በግልፅ ቦታ እስከ ቀበሌ ድረስ ለህብረተሰቡ በመለጠፍ  መመሪያና ደንቦች በግልፅ ቦታ ሳይ በማስቀመጥ ማንበብ የሚፈልግ ካለ አንብቦ የሚመልስበት ግልጽ የሆነ አሰራር በመዘርጋት  መልካም ተሞክር በማሌ ወረዳ ተሰርቷል፡፡
- ለግልፅኙነት አመቺ አሰራር ለመፍጠር በተደረገው ጥረት፤ ገንዘብ በቀበሌ በነጭ ወረቀት ይሰበሰብ የነበረው በካርኒ ሆኗል፣ የከፈሉ፣ ያልከፈሉ በግልጽ ይለጠፋል፡፡ ኃላፊነቱን ያልተወጣ የቀበሌ አመራር ህብረተሰቡ ገምግሞ ያስወግዳል /ለምሳሌ ቴሞቤል/፣ በሴክተር በጀት በደፋ ህብረተሰቡ ይለጠፋል ህብረተሰቡ የተለጠፈ በጀት ምን ሳይ እንደወለ ያያል፡፡ለዚህ አበረታች ተሞክሮ  ደቡብ አሪ ወረዳ ተጠቃሽ ነው፡፡

## 5. <u>ተጠያቂነት መርህን በተመለከተ</u>

- የተገባ ቃል በመጠበቅና በተገባው የራስ ቃል በመስራት ሥልጠና በመውሰድና ተግባራዊ በማድረግ ማሌ ወረዳ በቀበሌም ሆነ በወረዳ ሴክተር ጽ/ቤት ደረጃ የማይፈፀም ተስፋ አይሰጥም፡፡ተጠያቅነት መርሆ በመያዝ አገልጋይ ከተገልጋይ ከጌታው ድብቅ ሲሆን ስለማይችል ባለጉዳይ የሚፈልገው ሰው መኖር አለመኖሩን በር ሳይ በሚሰቀል ምልክት በማድረግ ይጦቅማሉ (አቅም ግንባታና ማስታወቂያ ጽ/ቤት ናቸው ይህን አሰራር የሚጠቀሙበት)፣በዞን ሴክቴር መ/ቤቶችም

## 6. <u>ፍትሃዊነት መርህን በተመለከተ</u>

- በመርሆ ሳይ ስልጠና በመስጠት  በህግ ፊት ሁሉም ሰው እኩል መሆናቸውን ተረድተው መብታቸውን በማስጠበቅ ግደታቸውን በመወጣት የህብረተሰቡ ግንዛቤ እንድያድግ በማድረግ በምንም ሁኔታ አድልዎ እንዳይፈጸም ከማድረግ ባሻገር ሁሉም ሰው እኩል መሆኑን  በተግበር በማሳየት የተራ መጠበቂያ ካርድ በመስጠት ባለጉዳይ በተራ እንድስተናገድ ፍትሃዊ በማድረግ ማሌ ወረዳ  መልካም ተሞክሮ አሰይቷል ፡፡

## 7. <u>የህግ የበላይነት መርሆን በተመለከተ</u>

- የህግ የበላይነት በመረዳት በተሰጠ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በመጠቀም ህብረተሰቡ መብቶችና ጥቅሞች በእኩልነት የሚጠበቅበት ከአድልዎ በፀዳ መልኩ በቀበሌያት ለማስፈን የሚሰሩ ስራዎችም ሆኑ ማንኛውም የቀበሌው ጉዳይ ውሳኔ የሚያገኘው በህዝቡ ብቻ መሆኑ በሁሉም ወረዳ እየተረጋገጠ መጥቷል፡፡

## 8. ቀልጠፋነትና ውጤታማነት መርህን በተመለከተ

- ❖ በመምሪያው በዕቅድና በሪፖርት ላይ ይመከርበታል፣በየጊዜውም ውጤቱ ይገመገማል፡፡ ለምመለከታቸውም ሪፖርት ተደርጓል፡፡
- ❖ ውስን ሃብት በመጠቀም መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ በሴክተሩ ተግባራዊ እንድሆን ጥረት ተደርጓል፡፡
- ❖ በሁሉም ወረዳ ዕቅዶች መፈፀማቸውን ለመከታተል ቼክ ሊስት በማዘጋጀት ክትትል ይደረጋል፣ የሥራ አፈፃፀም ግምገማ ይካሄዳል፣ የሪፎርም ውይይቶች ይካሄዳሉ፣ ሪፖርቶች ይገመገማሉ ችግር ካለ ማስተካከያ የሚደረግበት ሁኔታ ተመቻችቷል፡፡

## 2. በፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕረግራሞች የተፈጸሙ ዝርዝር ውጤቶች

- ❖ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም በተቀናጀ ሁኔታ ለማስተባበር የቴክኒክ ኮሚቴው የ2000 ዓ.ም ሥራውን ገምግሞ ለ2001 መሪ ዕቅድ ለማዘጋጀት ክፍተቶችን በመለየት ወደ ሥራ ገብቷል፡፡በሰሜን አሪ፣በበና ፀማይ፣በደቡብ አሪና በዳሳነች ወረዳ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ለመተግበርና ለማሻሻል በሚችል ዕቅድ ተዘጋጅቶ ውይይቶች ተደርጓል፡፡
- ❖ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም በተዘረጋ አሰራር ቀጣይነትና በቀላሉ ልደርስ የሚችል ማድረግ በማሌ ወረዳ በ22 ቀበሌያት፣በደቡብ አሪ በ49 ቀበሌያት፣በበና ፀማይ በ28 ቀበሌያት የፀጥታ ኮሚቴ በማቋቋም ሥራው እንድሰራ ድጋፍ ተደርጎ እየተሰራበት ነው፡፡
- ❖ በሐመር ወረዳ የፍትህ ሥራቱን ለማስተባበር ቼክ ሊስት ተዘጋጅቶ በወረዳው የሚገኙ የፍትህ አካላት ድጋፍ ተደርጎ ጠንካራና ደካማ ጎናቸው ተለይተው በማስቀመጥ የተሻለው አሰራር ያለበት ቦታ እንደ መልካም ተሞክሮ እንድወሰድ ጥረት ተደርጓል፡፡
- ❖ በፍትህ ሥርዓት ከሁሉም ወረዳዎች በማሌ ወረዳ የተሻለ አፈጻጸም በመሆናቸው ወደ ሁሉም ወረዳ ሊስፋፋ የሚገባቸው አፈጻጸሞች ተቀምሯል፡፡
- ❖ የፍትሕ አካላቱን ቅንጅታዊ አሠራር ማጠናከር ፖሊስ፣ ዐቃቤ ሕግ፣ ፍ/ቤትና ማረሚያ ቤት የሥራ ቅብብሎሽና ተመጋጋቢነት ያላቸው በመሆኑ የዜጐች ፍትሕ እንዳይጓደል አንዱ ከሌላው የሚፈልገው በቀላሉ የሚሟላበትን የቅንጅት አሠራር መፍጠር የሚከተሉት ዝርዝር ውጤቶች ቀርቧል፡፡

### 3.1 ፖሊስ ማሻሻያ ፕሮግራምን በተመለከተ

- ❖ በሁሉም ከተማና ገጠር ቀበሌዎች የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ እንዲጠናከር ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፡፡
- ❖ የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም በተቀናጀ ሁነታ ተግባራዊ ለማድረግ በማሌ ወረዳ በ15 ቀበሌያት ለሚገኙ ለ75 ማህበራዊ ፍርድቤት ዳኞች በፍትህ አሰጣጥ ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

እንዲሁም  ኮሙኒቲ ፖሊሲንግ ስማጠናከርና ስመደገፍ በየንዑስ ቀበሌው 5 አባላት የያዘ የፀጥታ ኮሚቴ ተደረጅተው የሥልጠና ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡

- በበና ፀማይ ወረዳ በሁሉም ቀበሌያት የኮሚዩኒት ፖሊስንግ እንዲጠናከር  ከፖሊስ አባሎች  ጋር በመቀናጀት ድጋፍና አገዛ 3ጊዜ  ተደርጓል፡፡

### 3.2 <u>የፍ/ቤት ማሻሻያ ፕሮግራምን  በተመለከተ</u>

- የፍ/ቤቶች ተደራሽነትና ቀጣይነት ሥራ በዘለቀታ ሁኔታ እንዲቀጥል ተዘዋዋር ችሎት በ4 ወረዳ በተጠናከረ ሁኔታ እየተካሄደ ነው፡፡ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት በቪድዮ ኮንፈራስ የዳኝነት ሥርዓቶችን ለማካሄድ ቅድመ ዝግጅት ሁነታዎች እየተሰሩ ነው፡፡
- በማሌ ወረዳ አስተማሪ የሆነን ውሳኔ በተመለከተ ጠለፋን፣ አስገድዶ መድፈርን በዕለቱ በቦታው ውሳኔ የሚሰጥበት ሁነታ ተመቻችቷል፡፡ የክስ ማመልከቻ ቅፃችን በማዘጋጀት ለማመልከቻ የሚወጣውን ወጪ መቀነስ ተችሏል፣የማስረጃ ስርዓት በአንድ ሳይ መቅረቡ በፊት ከማስረጃ በኋላ መከላከያ ይቀርብ የነበረውን አስቀርቷል፣ ከ8-10 ቀጠሮ የነበረው የቀጠሮ ብዛት ከ3-4 ቀጠሮ ሆኖ ዝቅ ብሏል፡፡

### 3.3 <u>የዓቃቤ ህግ ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራምን በተመለከተ</u>

- በደቡብ አሪ ወረዳ እጅ ከፍንጅ የሚያዙ ወንጀሎች ከ48 ሰዓት በፊት የሚጠረጠሩትን ግለሰብ ለህግ ለማቅረብ እንዲቻል መረጃ ተሰብስቦ በተባለው ጊዜ ለህግ እንዲቀርብ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

- በማሌ ወረዳ ረቂቅ በሆኑ ወንጀሎች ሳይ ለፖሊስ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ሰብዓዊ መብቶች ሳይጣሱ፣ ድብደባ ሳይፈፀም ምርመራ እንዲካሄድ ለፖሊስ  ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ቀጠሮ ለማሳጠር በተዘዋዋሪ ችሎት ይሰራል፣ ማስረጃም ተከሳሽም በአንድ ቀጠሮ ይቀርባሉ፣ በሚቀጥለው ቀጠሮ ውሳኔ የሚሰጥበት ሁኔታ ተመቻችቷል፡

### 3.4 <u>*የማረሚያ ቤቶች ማሻሻያ ንዑስ ኘሮግራምን* በተመለከተ</u>

- *ማረሚያ ቤቶች በፍትሕ አስተዳደር ሥርዓት የታራሚች/የእስረኞችን ሰብዓዊ መብት የመጠበቅ ኃላፊነት የተጣለበት ተቋም ሲሆን በማሻሻያ ንዑስ ኘሮግራሙ የታቀፉ ተግባሮች: ተገቢውን የመጠለያ፣ የምግብና የሕክምና አግልጋሎት እንዲያገኙ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓቱ* በተሟላ ሁኔታ እንዲዘረጋ ጥረት ተዘርግቷል፡፡

- *ታራሚዎች ባጠፉት ጥፋት ተጸጽተው ለወደፊቱ መልካምና አምራች ዜጋ ሆነው እንዲወጡ ማድረግ፣* /*በተለይም የቀለምና የሙያ ትምህርት በበቂ ሁኔታ እንዲያገኙ* ተደርጓል/

## 8. ኢኮቴ ልማት አቅርቦትና አገልግሎትን በተመለከተ የተፈፀሙ ዝርዝር ውጤቶች

- የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ማስፋፋትና በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት በአጠቃላይ ለ84 ሠልጣኞች መሠረታዊ የኮምፒውተር ስልጠና ተሠጥቷል :: የኢኮቴ ልማት አቅርቦትና አገልግሎት የስራ ሂደት ከዚህ በላይ ያሉትን መሰረታዊ የኮምፒውተር ሰልጣኞችን በየቢሮአቸው በመሄድ ክትትል እያደረገ ይገኛል፡፡
- የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሳሪያዎች ባሉበት በዞንና ወረዳዎች በመገኘት የኮምፒውተር ጥገናተደርጓል፣ በድምሩ 12800 ብር ልያወጣ የሚችለውን ወጪ ማዳን ተችሏ፡፡
- ቀበሌያትን የዘመናዊ መረጃ ልውውጥ ስርዓት ተጠቃሚ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት 70 ቀበሌያት በሰሜን አሪ፣ በደቡብ አሪ፣ በበና-ፀማይና በሀመር ዳሰነችና ኛንጋቶም ወረዳዎች የሽቦ አልባ ስልክ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡
- መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ለተገበሩ የሥራ ሂደቶችን ኮፒውቲራዝ ለማድረግ በተያዘው ዕቅድ መሠረት 10 ኮምፒውተር እና 30 እስካነሮች በዞን በ8 ወረዳዎችና በአንድ ከተማ አስተዳደር ተሰራጭቷል፡፡
- የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ማስፋፋትና በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት የሚደረገውን ጥረት ለመደገፍ በዞን ደረጃ የICT ስትሪንግ ኮሚቴ ተቋቁሟል

**የዕቅድ አፈፃፀም ደረጃ**

- ቁልፍ ውጤት 90 %
- አበይት ውጤት 80.85 %

## 3 በዕቅድ አፈፃፀም ወቅት የነበሩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች

### 5.1 ጠንካራ ጎን

ዕቅድን ለመፈፀም ያለ ተነሳሽነት ከፍተኛ መሆን፡፡ ዕቅዱ ቢዘገይም ባለፈው ዓመት በነበረ ዕቅድ መስራት መቻል፡፡

### 5.2 ደካማ ጎን

የ2001 ዕቅድ መዘግየትና እቅዱንና አዲሱን አሰራር ስርኣት ለውጥ ተግባራዊ ይደረጋል በማለት ለረጅም ጊዜ መጠባበቅ

## 6. በዕቅድ አፈፃፀም ወቅት ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች:-

- የበጀት በወቅቱ ያለመለቀቅ
- ክልል የ2001 ዓ.ም. ዕቅድን ማዘግየት

**የተወሰደ መፍትሔ እርምጃ ፣**

- ❖ በጀት የማይጠይቅ ስራዎችን መስራትና አነስተኛ ወጪን በግል በመሸፈን ስራው እንዳይቀር ማድረግ፤
- ❖ አዲሱ አቅድ እስኪመጣ ድረስ በቀድሞው አቅድ በመጠቀም መስራት፤
- ❖ ባሉት ሰራተኞች ሽፍኖ መስራት

<u>ትኩረት የሚሹ ጉዳዩች</u>

- ❖ በጀት ወቅቱን ጠብቆ በሀምሌ ወር ቢለቀቅ መልካም ነው፤
- ❖ በኢኮቴ የስራ ዘርፍ ባለሙያ በወቅቱ ቢቀጠር
- ❖ በዕቅድ መሠረት ተቀናጅቶና ወቅትን ጠብቆ መስራት ውጤት የሚያመጣ ይሆናል፡፡

*<u>ሪፖርቱን ያዘጋጀው</u>*

አቶ ---------------------------------

ፊርማ----------------------------

ቀን <u>1/08/2001 ዓ.ም.</u>

*<u>ሪፖርቱን ያፀደቀው</u>*

ስም --------------------------------

ፊርማ-----------------------------

ቀን <u>1/08/2001</u>